የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሀያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፴፪
አዲስ አበባ መጋቢት ፳፱ ቀን ፪ሺ፲፩

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

26th Year No. 32
ADDIS ABABA April 7th, 2020


**ማውጫ**


አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፹፫/፪ሺ፲፪ ዓ.ም

የፌደራል የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር ……………………………………………….....ገጽ ፲፪ሺ፬፻፸


**Content**


Proclamation No. 1183 /2020

Federal Administrative Procedure Proclamation Page…………………………………………12470


**አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፹፫/፪ሺ፲፪**

**የፌደራል የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓትን ለመደንገግ የወጣ አዋጅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት መንግስታዊ አሰራር ለሕዝብ ግልጽ በሆነ መንገድ መከናወን እንዳለበትና ማናቸውም የመንግስት ባለሥልጣን ኃላፊነቱን ሲያጓድል ተጠያቂ እንደሚሆን የተመለከተ በመሆኑ፤

የአስተዳደር ተቋማት በሰዎች መብቶችና ጥቅሞች ላይ የሚያስከትሉትን ጣልቃ ገብነት በሕግ የሚመራና ለሕግ የሚገዛ መሆኑን ማረጋገጥ በማስፈለጉ፤

**PROCLAMATION NO. 1183/2020**

**A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR FEDERAL ADMINISTRATIVE PROCEDURE**

**WHEREAS**, the Federal Democratic Republic of Ethiopia Constitution provides that the working procedure of the Government is to be transparent, and that any Public Official is held accountable for failure in his duties;

**WHEREAS**, it is necessary to regulate Administrative Agencies to refrain there intervention against people Rights and Interests;


ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

የአስተዳደር ተቋማት የውሳኔ አሰጣጥና የመመሪያ አወጣጥ መርሆዎችና ሥነ-ሥርዓት እንዲሁም በአስተዳደራዊ ውሳኔዎችና መመሪያዎች ቅር የተሰኘ ሰዉ የውሳኔዎቹንና የመመሪያዎቹን ሕጋዊነት በፍርድ ቤት የሚያስመረምርበት ሥርዓት በመደንገግ አስተዳደራዊ ፍትህን ማስፈን አስፈላጊ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### ፩ አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የፌደራል የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፹፫/፪ሺ፲፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ **“የአስተዳደር ተቋም”** ማለት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት አስፈጻሚ አካል ሆኖ በሕግ የተደራጀ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሲሆን ለፌደራል መንግሥት ተጠሪ የሆነ የከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን ይጨምራል፤

፪/ “**መመሪያ**” ማለት ሕግ አውጪው አካል በሚሰጠው የውክልና ስልጣን መሰረት በአስተዳደር ተቋም የሚወጣና በሰዎች መብት ወይም ጥቅም ላይ ውጤት የሚያስከትል የሕግ ሰነድ ሲሆን በስራ ላይ ያለ መመሪያን የሚያሻሽል ወይም የሚሽር የሕግ ሰነድንም ይጨምራል፤

**WHEREAS** it is necessary to guarantee administrative justice by promoting culture of transparency and accountability through legally establishing a system of judicial review for persons who might be aggrieved by acts of administrative agencies,in their rule-making and decision-making capacities,

**NOW THEREFORE**, in accordance with Article 55 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows .

## SECTION ONE

## GENERAL PROVISIONS

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as “Federal Administrative Procedure Proclamation No. 1183/2020.”

### 2. Definition

In this Proclamation, unless the context requires otherwise:

1/ **“Administrative Agency”** means an Executive Organ of the Federal Democratic Republic of Ethiopia duly established by law and includes the Executive Organs of City Administrations accountable to the Federal Government;

2/ **“Directive”** means a legislative document that is issued by an administrative agency based on delegation of Power bestowed up on it by the Legislator which affects people’s Rights and Interests. The term also includes the amendment, or repeal of an already existing directive;

፫/ **"የአስተዳደር ውሳኔ"** ማለት መመሪያ ማውጣትን ሳይጨምር የአስተዳደር ተቋም በዕለት ተዕለት ተግባሩ በሰዎች መብት ወይም ጥቅም ላይ የሚሰጠው የአስተዳደር ውሳኔ ነው፤

፬/ **"ሰው"** ማለት ማናቸውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፭/ በዚህ አዋጅ በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትን ጾታ ይጨምራል፡፡

**፫.<u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>**

፩/ ይህ አዋጅ በሁሉም የአስተዳደር ተቋማት ላይ ተፈፃሚ ሲሆን በወንጀል ሥነ ሥርዓት ህጉ በሚመሩ የዐቃቤ ህግ እና የፖሊስ ተግባራት እንዲሁም በመከላከያና፣ የደህንነት ተቋማት ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም ፣ እነዚህ ተቋማት፣ ከዋና ኃላፊነታቸው በተጓዳኝ ፣ አገልግሎት የመስጠትና የቁጥጥር ስራዎችን በተመለከተ፣ መመሪያ ሲያወጡ እና አስተዳደራዊ ውሳኔዎችን ሲወስኑ በዚህ አዋጅ መሰረት ይገዛሉ ።

፫/ የዚህ አዋጅ አንቀፅ ፲፩ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ብሄራዊ ባንክ የሀገሪቱን የውጪ ምንዛሬ ተመንና የወለድ ተመንን እና ሌሎች ተመሳሳይ ሚስጥራዊ ጉዳዮችን በተመለከተ መመሪያ ሲያወጣ በዚህ አዋጅ አንቀፅ ከ፯-፲ የተመለከቱትን ግዴታዎች ለመተግበር አይገደድም፡፡

3/ **"Administrative Decision"** means decision issued by an administrative agency on relating to persons rights or interest in its day-to-day function, excluding issuance of Directives;

4/ **"Person"** means any Natural or Juridical Person;

5/ Any expression in the masculine gender includes the feminine.

**3. <u>Scope of Application</u>**

1/ This Proclamation is applicable in all Administrative Agencies except Prosecutor and Police when they perform duties administered by the Criminal Procedure Law and Military and Security Institutions.

2/ Notwithstanding what is provided under Sub-article (1) of this Article, issuance of directives and decisions making relating to regulatory and service provision functions of these Institutions shall be subject to the requirements of this Proclamation.

3/ Without prejudice to Article 11 of this Proclamation, National Bank is not duty bound to implement obligations provided under Article 7-10 of this Proclamation when it enacts directives concerning exchange rate, interest rate of the country and other similar secret issues.

## ክፍል ሁለት

## የአስተዳደር መመሪያዎች

### ንዑስ ክፍል አንድ

### የመመሪያ መውጣት

**፬. መመሪያ ስለማውጣት**

፩/ ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም በሕግ በተሰጠው የውክልና ሥልጣን መሠረት መመሪያ ማውጣት ይችላል፡፡

፪/ የአስተዳደር ተቋም መመሪያ የሚያወጣው በዚህ አዋጅ በተደነገገው ሥነ-ሥርዓት መሠረት ብቻ ነው፡፡

፫/ ማንኛውም ሰዉ መብቱን ወይም ጥቅሙን በሚመለከት የአስተዳደር ተቋም መመሪያ ያላወጣ ቢሆንም የአስተዳደር ውሳኔ እንዲሰጠው የመጠየቅ መብት አለው፡፡

፬/ ማንኛዉም የአስተዳደር ተቋም ሊያወጣ የሚገባውን መመሪያ አለማውጣቱ በሕግ በተሰጠው ኃላፊነት ሊሰጥ የሚገባዉን አገልግሎት ወይም አስተዳደራዊ ዉሳኔ ላለመስጠት ምክንያት ሊሆን አይችልም፡፡

**፭. መመሪያ ስለሚወጣበት ጊዜ**

ማንኛዉም የአስተዳደር ተቋም ሊያወጣ የሚገባውን መመሪያ አስመልክቶ በእናት ህጉ መመሪያ እንዲወጣ በአስገዳጅ ሁኔታ በተደነገገ ጊዜ በሦስት ወራት ውስጥ አስገዳጅ ባልሆነ ሁኔታ በተደነገ ጊዜ ደግሞ በተገቢው ጊዜ ውስጥ መመሪያውን ማውጣት አለበት፡፡

**፮. መመሪያ እንዲወጣ ጥያቄ ስለማቅረብ**

፩/ ማንኛውም ሰው አንድ የአስተዳደር ተቋም ሊያወጣው የሚገባዉን መመሪያ በተገቢው ጊዜ ሳያወጣ ቢቀር መመሪያውን እንዲያወጣ በጽሁፍ ሊጠይቀው ይችላል፤

፪/ ጥያቄው የቀረበለት የአስተዳደር ተቋም በሠላሳ የሥራ ቀናት ውስጥ መመሪያውን የማውጣት ሂደት መጀመር ወይም ምክንያቱን በመግለጽ ጥያቄውን ውድቅ ማድረግ አለበት፡፡

## SECTION TWO

## ADMINISTRATIVE DIRECTIVES

### SUB SECTION ONE

### ISSUANCE OF DIRECTIVE

**4. Issuance of Directives**

1/ Any administrative agency can adopt directive on the basis of Power Delegated to it by Law.

2/ An adminstrative agency may issue directives only through the procedures provided by this Proclamation.

3/ Regarding matters affecting his right or interest, any person has the right to request an administrative aecision even though an administrative agency has not adopted a directive,

4/ Failure on the part of an adminstarative agency to issue Directives legally empowered to adopt shall not be a reason to deny services or rendering an Administrative Decision.

**5. Timely Adoption of Directives**

Any administrative agency shall issues a directive which is on the basis of mother law , If a directive is mandatory it shall be ratify within three month, If it is not mandatory it shall ratify with in a reasonable period of time.

**6. Petition for Adoption of Directives**

1/ Any person may ask the agency through written application to adopt a direcives, when an admistrative agency failed to adopt a directive it was mandated with in a reasonable period of time.

2/ An agency which receives a petition for adoption of a Directive shall commence the process of adopting a rule within 30 Days or deny the petition, stating its reasons.

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## የቅድመ መመሪያ አወጣጥ ሥነ-ሥርዓት

### ፯.የመመሪያ አወጣጥን የሚመለከት መዝገብ ስለማደራጀት

፩/ ማንኛዉም የአስተዳደር ተቋም የሚያወጣውን መመሪያ በተመለከተ የሚከተሉትን የያዘ መዝገብ ማደራጀት አለበት፦

ሀ) በተቋሙ በመታየት ላይ ያለ ረቂቅ መመሪያ ርዕሰ ጉዳይ እና የመመሪያውን አወጣጥ መርሃ ግብር፤

ለ) የረቂቅ መመሪያው ዝግጅት በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ የሚያመለክት መረጃ፤

ሐ) ረቂቅ መመሪያውን በተመለከተ የታተሙ ማስታወቂያዎች፤

መ) በረቂቅ መመሪያው ላይ አስተያየት ስለሚቀርብበት ጊዜ፤

ሠ) ረቂቅ መመሪያውን በተመለከተ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፰ እና ፱ መሠረት የተሰበሰቡ አስተያየቶችንና በአስተዳደር ተቋሙ በአስተያየቶቹ ላይ የተወሰዱ አቋሞችን፡፡

፪/ ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የሚደራጀውን መዝገብ መመልከት ወይም አስፈላጊውን ወጪ ሸፍኖ ቅጂውን መውሰድ ይችላል፡፡

### ፰ ·ማስታወቂያ ስለማዉጣት

የአስተዳደር ተቋም መመሪያ ከማውጣቱ በፊት ስለሚያወጣው ረቂቅ መመሪያ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ እና የተቋሙን ድረ ገጽ ጨምሮ በሌሎች የመገናኛ ብዙሃን የሚከተሉትን መረጃዎች የያዘ ማስታወቂያ ማውጣት አለበት፦

፩/ የመመሪያውን ረቂቅ ለማዘጋጀት መሰረት የሆነውን ሕጋዊ ሥልጣን እና በመመሪያው ስለሚካተቱት ርዕሰ ጉዳዮች፤

፪/ የረቂቅ መመሪያውን ቅጂ ማግኘት የሚቻል ስለመሆኑና የሚገኝበትን ሁኔታ፤

## SECTION TWO

## PROCEDURES BEFORE ADOPTION OF A DIRECTIVE

### 7. Keeping an Agency Record about Directives

1/ At the time of adopting a directive, an administrative agency shall keep a record/file containing the following:

a) The subject matter of the directive being considered and time line of major steps;

b) An information regarding the status of the draft directive in the process of adoption;

c) Notices published in relation to the adoption of the draft directive ;

d) A period of time with in which the public may comment on the draft ;

e) Comments received in accordance with Articles 8 and 9 of this Proclamation and positions taken regarding the comments.

2/ Any person may inspect or get a copy of the records organized in accordance with Sub Article (1) of this Article, against payment of expenses.

### 8. Noticing

An agency shall publish a notice containing the following information on a newspaper with wide circulation, its website and other media, prior to the adoption of a directive:

1/ The legal basis for to draft the law and the subject matters to be covered by the draft;

2/ Indicating that persons may get a copy of the draft and where they may access it;

፫/ በረቂቅ መመሪያው ላይ ሰዎች አስተያየታቸውን መቼ እና እንዴት ሊያቀርቡ እንደሚችሉ፤

፬/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፯ በተመለከተው መዝገብ ላይ የሰፈሩ መረጃዎችን የትና መቼ ማግኘት እንደሚቻል የሚገልፅ መረጃ፡፡

## ፱. <u>ረቂቅ መመሪያን ለአስተያየት ስለመላክ</u>

፩/ የአስተዳደር ተቋም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፰ በተደነገገው መሰረት ለሕዝብ ያሳወቀውን ረቂቅ መመሪያ ለሚመለከታቸው የአስተዳደር ተቋማትና ለሌሎች ባለድርሻ አካላት ለአስተያየት መላክ አለበት፡፡

፪/ የሚመለከታቸው የአስተዳደር ተቋማትና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በረቂቅ መመሪያው ላይ አስተያየት ካላቸው አስተያየታቸውን ተቋሙ በሚወስነው የጊዜ ገደብ ውስጥ በጽሁፍ መላክ አለባቸው፡፡ ተቋሙ የሚወስነው የጊዜ ገደብ በማናቸውም ሁኔታ ከ፲፭ የሥራ ቀናት ማነስ የለበትም።

## ፲. <u>የውይይት መድረክ ስለማዘጋጀት</u>

፩/ የአስተዳደር ተቋሙ በመመሪያው ረቂቅ ላይ የጽሑፍ አስተያየት መቀበያ ጊዜ ካበቃ በኋላ መመሪያው ከመፅደቁ በፊት ማንኛውም ሰው የሚሳተፍበት የውይይት መድረክ ማዘጋጀትና ግብዓት መሰብሰብ አለበት፡፡

፪/ ማንኛውም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፱ መሠረት ያልተስተናገደ በመድረኩ የሚሳተፍ ሰው አስተያየቱን በጽሑፍ ጭምር ሊያቀርብ ይችላል፡፡

፫/ የአስተዳደር ተቋሙ በሚያዘጋጀው የውይይት መድረክ ላይ አስተያየቶችን ማስተናገድ የሚያስችል በቂ ጊዜ መመደብ አለበት፡፡



3/ Where, when and how persons may give comments on the draft;

4/ Where, when and how persons may get access to the records kept in accordance with Article 7 of this Proclamation.

## 9. <u>Soliciting Comments on the Draft</u>

1/ An administrative agency shall solicit comments from relevant administrative agencies and other Stakeholders by sending the draft it publicized in accordance with Article 8 of this Proclamation.

2/ Agencies and stakeholders who may have comments on the draft should submit such comments in writing within a time prescribed by the agency. The period for comments to be prescribed by the agency shall not be less than 15 working days.

## 10. <u>Oral Hearing</u>

1/ After the expiry of the date for receiving written comments, the agency shall organize a public forum open for all interested persons and gather inputs.

2/ Persons who have not had the chance to given comments in accordance with Article 9, may submit written comments at the hearing.

3/ The agency shall ensure enough time is allotted for different views to be aired.

**፲፩. ከሥነ-ሥርዓት ነጻ ስለመሆን**

፩/ ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም መመሪያ ሲያወጣ በዚህ አዋጅ ከአንቀጽ ፯ እስከ ፲ ባሉት ድንጋጌዎች ከተመለከቱት ግዴታዎች በሚከተሉት ሁኔታዎች ነጻ ሊሆን ይችላል፡-

ሀ) የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ በመኖሩ በግዴታዎቹ ሥርዓት ውስጥ ለማለፍ ጊዜ የማይፈቅድ ሲሆን፣

ለ) ቅድመ ማስታወቂያ ማውጣቱ የሕዝብን ጥቅም የሚጎዳ ሆኖ ሲገኝ፣ ወይም

ሐ) ቅድመ ማስታወቂያ ማውጣቱ የመመሪያውን ተፈጻሚነት ፋይዳ ቢስ የሚያደርግ ሲሆን፡፡

፪/ የአስተዳደር ተቋም መመሪያ ሲያወጣ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ከግዴታ ነጻ እንዲሆን ያደረገውን ምክንያት የያዘ ዝርዝር መግለጫ ማዘጋጀት አለበት፡፡

**ንዑስ ክፍል ሦስት**

**መመሪያ ስለማጽደቅና ስለተፈፃሚነቱ**

**፲፪. መመሪያ ስለሚጸድቅበት ጊዜና ሁኔታ**

፩/ የአስተዳደር ተቋሙ በተዘጋጀው መመሪያ ረቂቅ ላይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፱ እና ፲ መሠረት የተወሰነው የጽሑፍ አስተያየት ማቅረቢያና የውይይት መድረክ ማካሄጃ ጊዜ እስኪያልፍ ድረስ መመሪያውን ማጽደቅ አይችልም፡፡

፪/ የአስተዳደር ተቋሙ መመሪያውን ከማጽደቁ በፊት በረቂቁ ላይ የቀረበ አስተያየት ከግምት ወስጥ ማስገባት አለበት።

፫/ የአስተዳደር ተቋሙ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተመለከተውን ግዴታ ለመወጣት በአስተያየቱ መሠረት ማስተካከያ ማድረግ አለበት ወይም አስተያየቱን የማይቀበል ከሆነ፣ የማይቀበልበትን ምክንያት የሚያብራራ ጽሑፍ ማዘጋጀት አለበት።

**11. Exemption from Procedures**

1/ An Agency may be exempted from the requirement provided under Articles 7 to 10 of this Proclamation where conditions listed hereunder are fulfilled :

a) Where there are emergencies and time does not allow to go through the requirements;

b) Where the issuance of advance notice may be contrary to Public Interest;

c) Where the issuance of notice may undermine the implementation of the directive;

2/ An agency issuing directives relying on Sub Article (1)of this Article shall prepare a record explaining the reasons justifying the exemption.

**SUB-SECTION THREE**

**RATIFICATION AND EFFECTIVENESS OF DIRECTIVES**

**12. Time and Manner of Ratifying Directive**

1/ An Agency may not ratify a Directive before the period for oral hearings and written submissions prescribed under Articles 9 and 10 expires.

2/ An agency shall consider comments submitted on the draft before ratifying a Directive.

3/ In fulfilling the obligation to consider indicated under Sub Article (2) of this Article, the agency may amend the draft in line with the comments or prepare a written justification for rejecting the comments.

፬/ የአስተዳደር ተቋሙ ረቂቅ መመሪያውን ከማጽደቁ በፊት ለአስተያየት ለፌደራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ መላክ አለበት፤

፭/ ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ በረቂቅ መመሪያው ላይ ያለውን አስተያየት በ፲፭ የሥራ ቀናት ውስጥ ለአስተዳደር ተቋሙ መላክ አለበት፡፡ ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ በዚህ የጊዜ ገደብ ውስጥ አስተያየቱን ካልላከ አስተያየት እንደሌለው ተቆጥሮ መመሪያውን የማጽደቁ ሂደት ይቀጥላል፡፡

## ፲፫. በመመሪያው ረቂቅና በሚወጣው መመሪያ መካከል ልዩነት ስለመኖር

፩/ የአስተዳደር ተቋሙ በማስታወቂያ ከተመለከተው ረቂቅ መመሪያ ጋር መሠረታዊ ልዩነት ያለው መመሪያ ማዉጣት አይችልም፤ ሆኖም መሠረታዊ ልዩነት ያለው መመሪያ ለማውጣት ከፈለገ የተጀመረውን የመመሪያ አወጣጥ ሂደት በማቋረጥና አዲስ የመመሪያ አወጣጥ ሂደት ከመጀመር አይከለከልም፡፡

፪/ በመጨረሻ መልክ የተዘጋጀ መመሪያ በማስታወቂያ ከተመለከተው የመመሪያው ረቂቅ መሠረታዊ ልዩነት አለው ሊባል የሚችለው በሚከተሉት ሁኔታዎች ነው፡-

ሀ) የረቂቅ መመሪያው የተፈጻሚነት ወሰን በጉልህ የተለወጠ ከሆነ፤ ወይም

ለ) ረቂቅ መመሪያው አዳዲስ ግዴታዎችን አካትቶ የተገኘ ከሆነ፡፡

## ፲፬. የማብራሪያ ጽሑፍ

ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም መመሪያ በሚያወጣበት ጊዜ የሚከተሉትን መረጃዎች የያዘ የመመሪያው ማብራሪያ ማዘጋጀት አለበት፡-

፩/ መመሪያው የወጣበት የሕግ መሠረትና ዓላማ፤

፪/ በማስታወቂያው የተሰራጨው ረቂቅና የመጨረሻ ሆኖ በወጣው መመሪያ መካከል የይዘት ልዩነት ካለ የተደረጉትን ለውጦች ከነምክንያቶቹ የሚገልጽ ማስታወሻ፤

4/ Prior to ratificaion of a Directive, the Agency shall send the draft to the Federal Attorney General for its opinion.

5/ The Attorney General shall submit its opinion within 15 working days. Where the Attorney General fails to submit its opinion within the time prescribed here, it shall be considered as though it does not have opinion on the draft and the agency may proceed to ratification.

## 13. Variance Between the Draft and Adopted Directive

1/ An Agency may not ratify a directive that is substantially different form the draft publicized through notice. However the Agency may not be barred from terminating the process at hand and commence a new one, where an agency intends to adopt a directive with substantial difference.

2/ A final draft directive shall be considered to be substantially different from the one publicized where:

a) The scope of application of the draft directive has markedly changed ;or

c) The draft directive introduces new obligations .

## 14. Explanatory Statement

At the time of adopting a directive, an agency shall prepare a directive explanatory note containing the following :

1/ The objective and legal basis for adoption of the directive;

2/ Where there are differences of content from the draft circulated through notice and the directive adopted, a note explaining the changes and the rationale thereof;

፫/ በረቂቅ መመሪያው ላይ የቀረቡ አስተያየቶችና የተወሰዱ እርምጃዎች ማጠቃለያ፡፡

**፲፭. <u>የመመሪያ ይዘትና ቅርፅ</u>**

፩/ በአስተዳደር ተቋም የሚወጣ ማንኛዉም መመሪያ የሚዘጋጀው በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋ ሲሆን ከመመሪያው ዋና ይዘት በተጨማሪ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፡-

ሀ) የመመሪያው ተራ ቁጥር፤

ለ) መመሪያው እንዲወጣ የሥልጣን ምንጭ የሆነውን ሕግ፤

ሐ) የመመሪያውን አጭር ርእስ፤

መ) ትርጓሜ፣ የተፈፃሚነት ወሰን፣ ዋና ዋና ድንጋጌዎች፤

ሠ) የማሻሻያ ፣ መሻሪያ፣ መሸጋገሪያ፣ ማቆያ ድንጋጌ ካለ ይህንኑ የሚመለከት ድንጋጌ፤

ረ) የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፰ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ መመሪያው የወጣበትንና ተፈጻሚ የሚሆንበትን ቀን፡፡

፪/ ማንኛውም መመሪያ በአጭርና በግልጽ ቋንቋ መጻፍ አለበት፡፡

፫/ የአስተዳደር ተቋም ሌላ አካል ያወጣቸውን በሥልጣኑ ክልል የሚወድቁ መመሪያዎች ወይም የሥነ-ምግባር ደንቦች በሙሉ ወይም በከፊል በማጣቀስ የራሱ መመሪያ አካል ማድረግ ይችላል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሰረት የመመሪያው አካል ያደረጋቸውን ሰነዶች ለሕዝብ ተደራሽ ማድረግና በአንቀጽ ፲፮ መሰረት እንዲመዘገብ ለፌደራል ጠቅላይ አቃቤ ሕግ መላክ አለበት፡፡

3/ A summary of comments on the draft and measures taken in accordance .

**15. <u>Content and Form of Directives</u>**

1/ In addition to the substantive body, a Directive adopted by an Agency shall be prepared in English and Amharic language and contain:

a) Serial Number of the Directive ;

b) A reference to a specific law on the basis of which the Directive is adopted ;

c) A short title of the Directive ;

d) Definition, scope of application, main Provisions;

e) A rule referring to directives amended repealed,transitory provisions or suspended if any;

f) Notwithstanding the date specified in Article 18 of this Proclamation the effective date of the Directive.

2/ Directives must be written in a precise and clear language .

3/ An agency may incorporate, by reference in its rules, all or part of directives or Code of conduct that has been adopted by another agency/body where these matters fall within its scope of power.

4/ The agency shall publicize rules it has incorporated pursuant to sub Article (3) of this Article and submit copies to the Federal Attorney General to be registered in accordance with Article 16 of this Proclamation.

**፲፮. <u>የመመሪያ ምዝገባ</u>**

፩/ ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም መመሪያ እንዳወጣ ተግባራዊ ከማድረጉ በፊት መመሪያውን ከነማብራሪያው ለፌደራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ በመላክ እንዲመዘገብ ማድረግ አለበት፡፡

፪/ ፌደራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሰረት የተላከለትን መመሪያ ቁጥር ሰጥቶ ይመዘግባል። መመሪያው ስለመመዝገቡም ለአስተዳደር ተቋሙ ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

፫/ የፌደራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ የመዘገበውን መመሪያ ከነማብራሪያው መዝግቦ ለአስተዳደር ተቋሙ ካሳወቀበት እለት ጀምሮ ለሕዝብ ክፍት ማድረግ አለበት፡፡

፬/ ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት በሥራ ላይ የነበረ መመሪያን ይህ አዋጅ በወጣ ከ፺ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለፌደራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ በመላክ እንዲመዘገብ ማድረግ አለበት፡፡

**፲፯ <u>የመመሪያ ተደራሽነት</u>**

፩/ የፌደራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፮ መሠረት የመዘገበውን መመሪያ በድህረ ገጹ ላይ መጫን አለበት፡፡

፪/ ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም ያወጣውን መመሪያ፦

ሀ) አሳትሞ ለሚመለከታቸው መንግስታዊና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ማሠራጨት፣ እና

ለ) በተቋሙ ድህረ ገጽ ላይ መጫን፣አለበት፡፡

፫/ ማንኛውም የመመሪያውን ቅጂ ማግኘት የሚፈልግ ሰው መመሪያውን ባለበት ሁኔታ የመመልከት ወይም ወጪውን ሸፍኖ ከአስተዳደር ተቋሙ የማግኘት መብት አለው፡፡

**16. <u>Filing of Directive</u>**

1/ Up on adoption, an agency shall before put on the directives it has sending the copies and accompanying explanatory statement to the Attorney General.

2/ The Federal Attorney General shall provide a serial identification number and record Directives submitted to it in accordance with sub-Article (1) of this Article. It shall also immediately notify the agency about the status of registration.

3/ The Attorney General shall publicize to the pubic a filled directives with its explanatory statement.Since the date of notifying its registration.

4/ All Agencies shall file directives they have adopted prior to the coming in to force of this Proclamation within 90 Days after the coming in to force of this Proclamation by sending copies to the Federal Attorney General .

**17. <u>Accessibility of Directives</u>**

1/ The Federal Attorney General shall post directives on its own website that has filed in accordance with Article 16 of this Proclamation.

2/ Any agency shall issued a directive :

a) Print and disseminate to Governmental and other Stakeholders ; and

b) Post it on its website .

3/ Any person who is interested can observe on the place situated or may get a copy of the directive subject to payment of expenses.

**፲፰ የመመሪያ ተፈጻሚነት**

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፮ መሠረት ያልተመዘገበ እና በአንቀጽ ፲፯ ንዑስ አንቀጽ (፪) ፊደል ተራ (ለ) መሠረት በአስተዳደር ተቋሙ ድህረ ገጽ ላይ ያልተጫነ መመሪያ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ተፈጻሚነቱን ያጣ መመሪያ ተፈፃሚነት እንዲኖረው በዚህ ክፍል ንዑስ ክፍል ሁለት የተደነገገውን የቅድመ መመሪያ አወጣጥ ሥነ-ሥርዓት ተከትሎ እንደ አዲስ እንዲወጣ ሊደረግ ይችላል፡፡

**፲፱. ስለመመሪያ ተፈጻሚነት ግምገማ**

ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም ያወጣውን መመሪያ አፈጻጸም በተመለከተ በየጊዜው እየገመገመ አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ አለበት፡፡

## ክፍል ሦስት

## የአስተዳደር ውሳኔዎች

## ንዑስ ክፍል አንድ

## የአስተዳደር ውሳኔ አጀማመር

**፳. የአስተዳደር ውሳኔ መጀመር**

፩/ የአስተዳደር ውሳኔ እንዲሰጥ የሚቀርብ ጥያቄ ጉዳዩ በሚመለከተው ሰው ወይም በወኪሉ ሊቀርብ ይችላል፡፡

፪/ የአስተዳደር ውሳኔ በሚመለከተው የአስተዳደር ተቋም አነሳሽነት ሊጀመር ይችላል፡፡

**፳፩. የአስተዳደር ውሳኔ ጥያቄ የሚቀርብበት ሁኔታ**

፩/ የአስተዳደር ውሳኔ ጥያቄ በጽሑፍ ሆኖ እንደሁኔታው በአካል፣ በተመዘገበ ፖስታ ወይም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ሊቀርብ ይችላል፡፡

፪/ የአስተዳደር ውሳኔ ይሰጥልኝ ጥያቄ አቤቱታ በፅሑፍ ሲቀርብ የሚከተሉትን መያዝ ይኖርበታል፡-

**18. Conditions of Enforcement**

1/ A directive that has not been filed pursuant Article 16 or posted on the website of the agency pursuant to Article 17 (2) (b) of this Proclamation may not be enforced

2/ A directive that has lost its validity in accordance with sub Article (1) of this Article may be adopted following the Procedures provided under this Sub Section of Two of this Section of Proclamation.

**19. Periodic Review of Directives**

An Agency shall from time to time review the implementation of directives it has adopted and take necessary measures.

## SECTION THREE

## ADMINISTRATIVE DECISIONS

## SUB SECTION ONE

## INITIATION OF ADMINISTRATIVE DECISIONS

**20. Initiation of Administrative Decision**

1/ An application for an administrative decision be made by an interested person or his agent.

2/ An administrative decision process may be initiated by the relevant administrative agency.

**21. Manner of Administrative Decision Application**

1/ An application for administrative decision shall be made in writing and may be submitted in person, a registered postal address or electronic means.

2/ A written application of administrative decision shall include:

ሀ) ቀን፣ የአቤቱታ አቅራቢው ወይም ወኪሉ ስም፣ ፊርማ እና አድራሻ፤

ለ) አስተዳደራዊ ተግባሩን የሚፈፅመው ተቋም ስም፤

ሐ) የአቤቱታ አቅራቢው መብት ወይም ጥቅም፤

መ) ተቋሙ ሊፈፅመው የሚገባ አስተዳደራዊ ተግባር፤

ሠ) ተቋሙ ለሚተገብረው አስተዳደራዊ ተግባር መሰረት የሆኑ ምክንያቶች እና ተያያዥ ማስረጃዎች፤

፫/ የአስተዳደር ተቋም የአስተዳደር ውሳኔ ጥያቄ የሚቀርብበትን ቅጽ ሊያዘጋጅ ይችላል፡፡

**፳፪. ጥያቄን የመቀበል ማስረጃ**

፩/ አቤቱታ የቀረበለት ተቋም አቤቱታውን በተረከበበት ጊዜ አቤቱታውን የተቀበለ መሆኑን መዝግቦ የማረጋገጫ ጽሑፍ መስጠት አለበት፡፡

፪/ የማረጋገጫ ጽሑፉ አቤቱታውን የተቀበለ መሆኑንና ከአቤቱታው ተያይዘው የቀረቡ ሰነዶችን ዝርዝር የሚያሳይ መሆን አለበት፡፡

**ንዑስ ክፍል ሁለት**

**የአስተዳደር ውሳኔ አሰጣጥ መርሆዎች**

**፳፫.የአስተዳደር ውሳኔ የሚሰጠው ሰው**

የአስተዳደር ውሳኔ የሚሰጠዉ ሰው የአስተዳደር ተቋሙ የበላይ ኃላፊ ወይም ሥልጣን የተሰጠዉ የተቋሙ የሥራ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ ብቻ መሆን አለበት፡፡

**፳፬.በሕግ የተሰጠ ሥልጣን ወሰንን አለማለፍ**

የአስተዳደር ውሳኔ የሚሰጠዉ ሰዉ ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ ለአስተዳደር ተቋሙ በሕግ የተሰጠውን ሥልጣን ወሰን ማለፍ የለበትም፡፡

**፳፭.የግል እና የሕዝብ ጥቅምን ማመዛዘን**

የአስተዳደር ውሳኔ የሚሰጠዉ ሰዉ የአስተዳደር ተቋሙን ተገልጋይ የግል ጥቅም እና በአስተዳደር ተቋሙ ዓላማ የተመለከተውን የሕዝብ ጥቅም ማመዛዘን አለበት፡፡

a) Date, name of the applicant or his agent, signature and address;

b) Name of the administrative agency to whom the petition is made;

c) The right and interest of the applicant being sought;

d) Act that the administrative authority has to do.

e) Facts and evidence relevant for the decision.

3/ An agency may prepare forms through which an application may be made.

**22. Record of Applications**

1/ Upon receiving an application for administrative decision, the agency shall immediately furnish.

2/ A written confirmation of application, shall contain details of receiving relevant documents attached there.

**SUB SECTION TWO**

**PRINCIPLES OF ADMINISTRATIVE DECISION MAKING**

**23. An Administrative Decision Maker**

decision may only be rendered by the Head or Authorized Official/Manager or Staff of an agency.

**24. Respecting Scope of Authority**

A person rendering an administrative decision shall respect the scope of authority of the agency established by Law.

**25. Balancing of Public and Individual Interest**

A person rendering an administrative decision shall balance the individual interest of the person regarding whom an administrative decision is being considered with that of the public interest identified in the objectives of the agency.

**፳፮.<u>አግባብነት በሌለዉ ጉዳይ ወይም ፍላጎት አለመመራት</u>**

የአስተዳደር ውሳኔ የሚሰጠዉ ሰዉ ለጉዳዩ አግባብነት በሌለዉ ጉዳይ ወይም ፍላጎት መመራት የለበትም፡፡

**፳፯.<u>ሙያዊ ውሳኔ መስጠት</u>**

የአስተዳደር ውሳኔ የሚሰጠዉ ሰዉ ሙያዉ የሚጠይቀዉን ሥነ-ምግባር፣ ትጋት እና ጥንቃቄ ማክበር አለበት፡፡

**፳፰.<u>ማዳመጥ</u>**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፫ መሠረት የአስተዳደር ውሳኔ የሚሰጠዉ ሰዉ የአስተዳደር ውሳኔ ከመሥጠቱ በፊት የሚመለከተዉን ሰው ፍሬ ነገር እና ማስረጃ በሚገባ ማዳመጥ እና መመርመር እንዲሁም እንደነገሩ ሁኔታ የሦስተኛ ወገን ተቃዋሚን እና የሕዝብን አስተ‹የየት ማዳመጥ አለበት፡፡

**፳፱.<u>በቅን ልቦና መወሰን</u>**

የአስተዳደር ውሳኔ የሚሰጠዉ ሰዉ በቅን ልቦና መወሰን አለበት፡፡

**፴.<u>በቂ ምክንያት መስጠት</u>**

የአስተዳደር ውሳኔ የሚሰጠዉ ሰዉ ለአስተዳዳር ውሳኔው በቂ ምክንያት መስጠት አለበት፡፡

**፴፩.<u>የጥቅም ግጭትን ማስቀረት</u>**

የአስተዳደር ውሳኔ የሚሰጠዉ ሰዉ ከተገልጋዩ ጋር የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለው ከሆነ ወይም በማናቸውም ሁኔታ የጥቅም ግጭት የሚያስከትልበት ከሆነ ጉዳዩን ከማየት እራሱን ማግለል አለበት፡፡

**፴፪.<u>የተገልጋዮችን እኩልነት ማክበር</u>**

የአስተዳደር ውሳኔ የሚሰጠዉ ሰዉ ሁሉንም ተገልጋዮች በዘር፣ በብሄር፣ በቀለም፣ በጾታ፣ በቋንቋ፣ በሀይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከት፣ በማህበራዊ አመጣጥ፣ በሀብት መጠን፣ በትውልድ ሁኔታ ወይም በሌላ ምክንያት ልዩነት ሳያደርግ መወሰን አለበት፡፡

**26. <u>Avoiding Irrelevant Matters and Interests</u>**

A person rendering an administrative decision should avoid influence from irrelevant facts or interests.

**27.<u>Rendering of Professionalsm</u>**

A decision, shall abide by the ethical standards, show due diligence and care that is required by the relevant task or profession.

**28. <u>Hearing</u>**

The person rendering administrative decisions in accordance with articles 23 of this Proclamation shall provide adequate opportunity of hearing to arguments and evidence presented by the person regarding whom decision is being made, and as the case may be to third parties as well as the public.

**29. <u>Good faith</u>**

A person rendering administrative decisions should made the decision in good faith.

**30. <u>Reasoned Decision</u>**

The person rendering administrative decisions should provide adequate reason for the decision he makes.

**31. <u>Avoiding Conflict of Interest</u>**

Where a person rendering administrative decisions has blood, affinity or any other kind of relation that may cause a conflict of interest, he shall recuse himself from case.

**32. <u>Keep Customers Equality</u>**

A person rendering administrative decisions shall not discriminate between persons based on race, color, ethnicity, sex, language, religion, political view, social background, class, or any other ground.

**፴፫. <u>በተገቢዉ ጊዜ መወሰን</u>**

፩/ የአስተዳደር ውሳኔ የሚሰጠዉ ሰዉ የአስተዳደር ውሳኔዉን ሳይዘገይ በተገቢዉ ጊዜ መስጠት እና በጉዳዩ ዙሪያ ያሉ ጥቅሞች በውሳኔው መዘግየት ምክንያት ለጉዳት እንዳይጋለጡ ማድረግ አለበት፡፡

፪/ የአስተዳደር ውሳኔ በተገቢው ጊዜ ሳይሰጥ መቅረት የአስተዳደር ውሳኔ ጥያቄውን ውድቅ በማድረግ እንደተሰጠ ውሳኔ ይቆጠራል፡፡

**፴፬.<u>ተገማች መሆን</u>**

የአስተዳደር ውሳኔ የሚሰጠዉ ሰዉ በፍሬ ነገር ተመሳሳይ የሆኑ ጉዳዮችን በተመሳሳይ ሁኔታ መወሰን አለበት፡፡

**፴፭ .<u>ግልጽ መሆን</u>**

የአስተዳደር ውሳኔ የሚሰጠዉ ሰዉ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቱ ግልጽነትን የተከተለ እንዲሆን ማድረግ አለበት፡፡

**<u>ንዑስ ክፍል ሦስት</u>**

**<u>ጉዳዩን ስለመስማት</u>**

**፴፮. <u>ጉዳዩን ስለመስማት</u>**

፩/ ማንኛውም አስተዳደራዊ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት ጉዳዩ በሚገባ መሰማት አለበት፡

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተጠቀሰው ቢኖርም ጉዳዩን መስማት ሳያስፈልግ ውሳኔመስጠትየሚቻለው፡-

ሀ) የፍሬ ነገር ክርክር ከሌለ፤

ለ) ልዩ መብት ከሆነ ወይም የአስተዳደር ተቋሙ በህግ በአማራጭ እንዲወስን ስልጣኑ ካለው፤ወይም

ሐ) አስቸኳይ ድርጊት ከሆነ፤ነው፡፡



**33. <u>Timely Decision</u>**

1/ The person rendering administrative decision shall give a decision without delay in a reasonable period of time and ensure that interests associated with the decision are not negatively affected as a result of delay.

2/ Failure to render decision within an appropriate period of time shall be considered as denial of the petition.

**34. <u>Predictability</u>**

In matters involving similar facts, the person rendering an administrative decision shall decide in the same manner.

**35. <u>Transparency</u>**

A person rendering administrative decisions shall ensure the transparency of the decision making process.

**<u>SUB SECTION THREE</u>**

**<u>HEARING THE ISSUE</u>**

**36. <u>Hearing of the Case</u>**

1/ Before rendering any administrative decisions shall provide adequate opportunity of hearing.

2/ Notwithstanding to sub article 1 of this Article decision may render without hearing:-

a) If there is no arguments of the facts of the case;

b) If it is special privilege or if the administrative agency has alternative decision power ;or

c) The issue is urgent.

**፴፯. ጉዳዩ ስለሚሰማበት አግባብ**

፩/ የአስተዳደር ጉዳይ በሚሰማበት ጊዜ ባለጉዳዩ በክርክሮች ሂደት ሁሉ ተገኝቶ ፡-

ሀ) ምስክርነት የመስጠት፤

ለ) ምስክሮችን እና ሌሎች ማስረጃዎችን የማቅረብ እና የማሰማት፤

ሐ) ለተቋሙ የቀረቡ ማስረጃዎችን የመስማትና የመመርመር፤መብት አለው፡፡

፪/ ተቋሙ ማስረጃ ለማግኘት በክርክሩ ተካፋይ ከሆነ ወገን፣ ከምስክሮች፣ ሙያዊ አስረጂ፣ የሰነድ ምርመራ እና ሌሎች ማናቸውንም አስፈላጊ ማስረጃዎችን ለማግኘት ሕጋዊ ዘዴዎችን መጠቀም ይችላል፡፡

**፴፰. ስለመነሳት**

፩/የአስተዳደር ውሳኔ የሚሰጥ ሰው በሚከተሉት ምክንያቶች ጉዳዩን ከማየት ሊነሳ ይችላል፡-

ሀ) ከጉዳዩ ላይ ቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ ጥቅም ካለው፤

ለ) ጉዳዩ የስጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ወይም በቅርብ የሚታወቅ ወዳጁ ሲሆን ወይም የእነዚህ ሰዎች የጥቅም ግጭት ያለበት ጉዳይ ከሆነ ፤

ሐ) በመታየት ላይ ላለው ጉዳይ እንደ ባለሙያ፣ ወኪል ወይም የግል ጠበቃ ሆኖ ተሳትፎ ከሆነ፤

መ) በመታየት ላይ ያለው ጉዳይ ሰራተኛው በስር ውሳኔ አይቶት በይግባኝ የቀረበለት ከሆነ፤

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተመለከቱ ምክንያቶች ካሉ ውሳኔ በሚሰጠው ሰራተኛ አነሳሽነት ወይም ጉዳዩ በሚመለከተው ሰው አመልካችነት ጉዳዩን ከማየት ሊነሳ ይችላል፤

**37. Conditions of Hearing**

1/ The parties to case has the right to appear in person and have the right:

a) To give testimony ;

b) To produce evidences ;

c) To access and examine evidences presented to the Authority .

2/ The Agency may use all legal methods to get documents of investigation and other any evidences from the party participated in the argument, witnesses and professional persons.

**38. Recusal**

1/ A person may be recused from the decision making on one of the grounds listed here under:

a) He has a direct or indirect interest on the matter ;

b) The matter at hand affects a person that has a relation with a decision maker in consanguinity or Affinity, close friend ;

c) If he has represented the person regarding whom the decision is being considered, as an agent, attorney or in any other professional capacity ;

d) He has made a decision on the matter in another capacity ;

2/ In case where one of the grounds listed under sub article (1) of this Article are present, the person may be recused from decision making process on his own accord, or the petition of the an interested person;

፫/ የይነሳልኝ ጥያቄ ከቀረበና ጥያቄው የቀረበለት ኃላፊ የመጨረሻ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ እንዲነሳ ጥያቄ የቀረበበት ሰራተኛ ውሳኔ ከመስጠት ሂደቱ ታግዶ ይቆያል፤

፬/ የእነሳለሁ ወይም የይነሳልኝ ጥያቄ የቀረበለት ኃላፊ በአምስት የስራ ቀናት ውስጥ ሰራተኛው ከውሳኔ ሰጪነት እንዲነሳ ወይም እንዲቀጥል መወሰን አለበት፡፡

## ንዑስ ክፍል አራት
## የአስተዳደር ውሳኔ

### ፴፱. የአስተዳደር ውሳኔውን ለተገልጋዩ ስለመስጠት

ማንኛውም የአስተዳደር ውሳኔ ከነምክንያቱ ለተገልጋዩ በጽሑፍ መሠጠት አለበት፡፡

### ፵. የአስተዳደር ውሳኔ

ማንኛውም የአስተዳደራዊ ውሳኔ በጽሑፍ ሆኖ የሚከተሉትን መያዝ ይኖርበታል፡-

፩/ የውሳኔ ቀንና ቁጥር ፤

፪/ የተቋሙን ስም ፤

፫/ በክርክሩ ተካፋይ የሆኑ ወገኖችን አድራሻ፤

፬/ አከራካሪ ፍሬ ነገር፤

፭/ የማስረጃዎች ትንተና፤

፮/ የፍሬ ነገር እና የሕግ ትንታኔ፤

፯/ ውሳኔ

### ፵፩. ስለ እገዳ

፩/ የአስተዳደራዊ ውሳኔ ወዲያውኑ መፈፀም በመብቱ ወይም በጥቅሙ የማይመለስ ጉዳት የሚያደርስበት ሰው ወሳኔው እንዲታገድለት ውሳኔውን ለሰጠው ተቋም አቤቱታ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሰረት አቤቱታ የተቀበለ የአስተዳደር ተቋም እንደየሁኔታው ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ ወይም የውሳኔውን ማናቸውም ክፍል ሊያግደው ይችላል፡፡

3/ If recusal is requested, until the head of administrative decision rendering final decision the person raised matter of recusal shall remain suspended from entertaining the case;

4/ The Head accepted the recusal request initiated by the interested person or others shall render decision within five working days to stay or recused .

## SUB-SECTION FOUR
## ADMINISTRATIVE DECISION

### 39. Giving the Decision to the Client

An Agency shall notify the concerned person of its decision with its reason in writing.

### 40. Administrative Decision

All administrative decision shall be made in writing and contain:

1/ Date and Number of Decision;

2/ Name of the Authority;

3/ Parties to the case and their address;

4/ Issues of claim;

5/ Discretion of Evidences;

6/ Description of Fact and Law;

7/ Decision.

### 41. Suspension

1/The party whose who may incur irreparable on his right and intrerest by immediate enforcement of the decision can apply for the suspension of the decision to the authority rendering decision.

2/ An administrative agency receiving a petition as per Sub Article 1 of this Article may order the case to be seen again or to suspend any part of the decision.

**፵፪. <u>የአስተዳደር ውሳኔን የሚፈጽመው ሰው</u>**

ማንኛውም የአስተዳደር ውሳኔ የሚፈጸመው ውሳኔውን በሰጠው ሰዉ ወይም በሚመለከተዉ አካል ይሆናል፡፡

**<u>ንዑስ ክፍል አምስት</u>**

**<u>በአስተዳደር ውሳኔ ላይ ስለሚቀርብ ቅሬታ</u>**

**፵፫. <u>ቅሬታ የማቅረብ መብት</u>**

ማንኛውም ሰዉ በተላለፈበት የአስተዳደር ውሳኔ ላይ ለአስተዳደር ተቋሙ ቅሬታ የማቅረብ መብት አለው፡፡

**፵፬. <u>የቅሬታ ማስተናገጃ አካል ማቋቋም</u>**

ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም የቅሬታ ማስተናገጃ አካል ማቋቋም እና ይህንኑ ለተገልጋዮች ይፋ ማድረግ አለበት፡፡

**፵፭. <u>የአስተዳደር ውሳኔው አፈፃፀም መታገድ</u>**

ማንኛውም ቅሬታ የቀረበበት የአስተዳደር ውሳኔ ቅሬታው ተመርምሮ እስኪወሰን ድረስ አይፈጸምም፡፡ ሆኖም የውሳኔው ሳይፈጸም መቆየት በሕዝብ ላይ የማይመለስ ጉዳት የሚያስከትል ከሆነ የአስተዳደር ተቋሙ የበላይ ኃላፊ ዉሳኔዉ እንዲፈጸም ሊያዝ ይችላል፡፡

**፵፮. <u>ቅሬታውን ስለመመርመርና ስለመወሰን</u>**

፩/ የአስተዳደር ተቋሙ የቅሬታ ማስተናገጃ አካል ቅሬታውን በሚገባ መመርመር እና የዉሳኔ ሀሳብ ለአስተዳደር ተቋሙ የበላይ ኃላፊ ወይም እሱ ለወከለዉ የሥራ ኃላፊ ማቅረብ አለበት፡፡

፪/ የአስተዳደር ተቋሙ የበላይ ኃላፊ ወይም እሱ የወከለዉ የሥራ ኃላፊ በቅሬታ ማስተናገጃ አካል የቀረበለትን የውሳኔ ሀሳብ ተመልክቶ የሰጠው ውሳኔ የተቋሙ የመጨረሻ ውሳኔ ይሆናል፡፡

**42. <u>Person to Enforce Administrative Decisions</u>**

An administrative decision shall be enforced by the person or a concerned body who has made the decision.

**<u>SUB SECTION FIVE</u>**

**<u>COMPLAINT AGAINST ADMINISTRATIVE DECISION</u>**

**43. <u>Right to Lodge Complaint</u>**

Any person against whom and administrative decision is made has the right to lodge a complaint to the Agency.

**44. <u>Establishment of Complaint Handling Body</u>**

All administrative agencies shall establish a complaint handling division and notify such establishment to clients.

**45. <u>Stay of Enforcement</u>**

Enforcement of any decision of an administrative agency against which a complaint is lodged will be stayed until the complaint is processed and a final decision made. However, the head of the Agency may order the enforcement of the decision where delay in enforcement may cause an irreversible damage to public interest.

**46. <u>Considering the complaint</u>**

1/ The complaint handling body shall properly examine the complaint it has received and present its recommendation to the Head of the Agency or an officer duly authorized by the Head.

2/ The decision of the Head of the Agency or an officer duly authorized by the Head of the Agency, after considering the recommendation of the complaint handling body shall be considered as the final decision of the agency.

**፵፯. ውሳኔውን ለተገልጋዩ ስለማሳወቅ**

የአስተዳደር ተቋሙ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፮ መሠረት የተሰጠውን ውሳኔ ወዲያዉኑ ለቅሬታ አቅራቢው በጽሑፍ መስጠት አለበት፡፡

**ክፍል አራት**

**በፍርድ ቤት የሚደረግ የአስተዳደር መመሪያዎችና ውሳኔዎች ክለሳ**

**ንዑስ ክፍል አንድ**

**የክለሳ አጀማመር**

**፵፰. የክለሳ አቤቱታ ስለማቅረብ**

የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፮ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፦

፩/ ማንኛውም ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው የአስተዳደር መመሪያ በፍርድ ቤት እንዲከለስ አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፤

፪/ ማንኛውም በአስተዳደር ውሳኔ ጥቅሙ የተነካበት ሰው ውሳኔው በፍርድ ቤት እንዲከለስ አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፡፡

**፵፱. የክለሳ አቤቱታ ስለሚቀርብበት ፍርድ ቤት**

፩/ የአስተዳደር መመሪያ ወይም ዉሳኔ እንዲከለስ አቤቱታ የሚቀርበው ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይሆናል፡፡ ፍርድ ቤቱ የሚሰጠው ውሳኔም የመጨረሻ ይሆናል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም፣ የአስተዳደር መመሪያን በተመለከተ ከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ወሳኔ፣ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሊቀርብበት ይችላል።

፫/ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የክለሳ አቤቱታዎችን የሚያስተናግድ የአስተዳደር ጉዳይ ችሎት ያደራጃል፡፡

**47. Notification of Decisions**

An agency shall notify the petitioner, in writing, the decision made pursuant to Article 46 of this Proclamation.

**SECTION FOUR**

**JUDICIAL REVIEW OF DIRECTIVES AND ADMINISTRATIVE DECISIONS**

**SUB-SECTION ONE**

**INITIATION OF REVIEW**

**48. Filing of Petition for Review**

Without prejudice to the Provisions under Article 46 of this Proclamation :

1/ Any interested person may file a petition requesting a judicial review of a directive;

2/ Anyone whose interest is affected by an administrative decision may file a petition requesting judicial review.

**49. Power of Review**

1/ A petition to review directives or administrative decisions shall be submitted to the Federal High Court and the decision of the Court will be final.

2/ Notwithstanding the stipulation under Sub- article (1) of this Article, a decision of High Court directive may be appealed to the Federal Supreme Court.

3/ The Federal High Court shall establish special benches dedicated to handle petitions for judicial review of administrative acts.

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## የክለሳ መርሆዎች

### ፶. የክለሳ ምክንያት

፩/ የአስተዳደር መመሪያ በፍርድ ቤት የሚከለሰው:-

ሀ) በዚህ አዋጅ ክፍል ሁለት የተመለከቱትን የሥነ-ሥርዓት ድንጋጌዎች ሳይከተል የወጣ መሆኑ ሲረጋገጥ፣

ለ) ከአስተዳደር ተቋሙ የሥልጣን ገደብ ውጪ የወጣ ሲሆን፣ ወይም

ሐ) በእርከን ከመመሪያ በላይ ከሆኑ ሌሎች ህጎች የሚቃረን ሲሆን ነው፡፡

፪/ የአስተዳደር ውሳኔ በፍርድ ቤት የሚከለሰው በዚህ አዋጅ ክፍል ሦስት የተደነገጉትን መርሆዎች የጣሰ ሲሆን ነው፡፡

### ፶፩. የክለሳ አቤቱታ የሚቀርበው በመጨረሻ ውሳኔ ላይ ስለመሆኑ

ማንኛውም የፍርድ ቤት ክለሳ አቤቱታ የሚቀርበው የመጨረሻ በሆነ የአስተዳደር ውሳኔ ላይ ብቻ ነው፡፡

### ፶፪. አስተዳደራዊ መፍትሄዎችን አሟጦ ስለመጨረስ

፩/ በሕግ በሌላ ሁኔታ ካልተደነገገ በቀር ማንኛውም ለፍርድ ቤት የክለሳ አቤቱታ የሚያቀርብ ባለጉዳይ አቤቱታውን ከማቅረቡ በፊት በአስተዳደር ተቋሙ ውስጥ ያሉትን አስተዳደራዊ መፍትሄዎች አሟጦ መጨረስ አለበት፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ድንጋጌ (፩) ቢኖርም የአስተዳደር ተቋሙ አስተዳደራዊ መፍትሄ የመስጠቱን ሂደት ከሚገባው ጊዜ በላይ ያራዘመ እንደሆነ አስተዳደራዊ መፍትሄ አሟጦ መጨረስ ግዴታ አይሆንም፡፡

## SUB-SECTION TWO

## PRINCIPLES OF REVIEW

### 50. Grounds of Review

1/ A Directive will be revoked by the Court where

a) It is proved to have failed to comply with the procedural rules provided in Chapter Two of this Proclamation;

b) It is ultravires; or

c) It is contrary to other laws placed higher in the Hierarchy of Laws.

2/ An administrative decision may be revoked if it is made in violation of the Principles provided under Chapter Three of this Proclamation.

### 51. Petition of Review of Decisions

A Judicial Review may only be sought against a final decision of an agency.

### 52. Exhaustion of Remedies

1/ Unless otherwise provided by law, a petitioner for Judicial Review is required to exhaust all remedies available within the Agency before petitioning the court for judicial review.

2/ Notwithstanding the rule under Sub Article (1) of this Article, where there is an undue delay on the part of the agency to provide remedies, the obligation to exhaust remedies will not apply.

## <u>ንዑስ ክፍል ሦስት</u>

## <u>የክለሳ ሥርዓት</u>

**፶፫. <u>የክለሳ አቤቱታ የሚቀርብበት ጊዜ</u>**

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ሀ) መሠረት የአስተዳደር መመሪያ በፍርድ ቤት እንዲከለስ የሚቀርብ አቤቱታ መመሪያው ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር የ፺ ቀናት ጊዜ ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡

፪/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶ ንዑስ አንቀጽ ፩ ፊደል ተራ(ለ) ወይም (ሐ) መሠረት የአስተዳደር መመሪያ በፍርድ ቤት እንዲከለስ የሚቀርብ አቤቱታ በማናቸውም ጊዜ ሊቀርብ ይችላል፡፡

፫/ የአስተዳደር ውሳኔ በፍርድ ቤት እንዲከለስ የሚቀርብ አቤቱታ ባለጉዳዩ ውሳኔውን እንዲያውቀው ከተደረገበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር የ፴ ቀናት ጊዜ ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡

**፶፬. <u>የጽሑፍ መልስ ስለማቅረብ</u>**

የክለሳ አቤቱታ የቀረበለት ፍርድ ቤት አቤቱታው ሊመረመር ይገባል ብሎ ሲያምን ቅሬታው የቀረበበት የአስተዳደር ተቋም በ፲፭ የሥራ ቀናት ዉስጥ የጽሑፍ መልስ እንዲሰጥ ያዛል።

**፶፭. <u>ሰነዶችን ስለማቅረብ</u>**

የክለሳ አቤቱታ የቀረበበት የአስተዳደር ተቋም አቤቱታ የቀረበበትን መመሪያ ወይም ዉሳኔ በተመለከተ አስፈላጊ ሰነዶች እንዲያቀርብ ፍርድ ቤቱ ሊያዝ ይችላል፡፡

## <u>SUB-SECTION THREE</u>

## <u>PROCEDURE OF JUDICIAL REVIEW</u>

**53. <u>Period of Limitation on Petition for Judicial Review</u>**

1/ A petition under Article 50 Sub Article 1 (a) to review a directive shall be submitted within 90 days after the adoption of the directive.

2/ A petition under Article 50 Sub Article 1 (b) or (c) to review a directive can be submitted any time.

3/ A petition to review an administrative decision shall be made within 30 days after the petitioner was notified of the decision .

**54. <u>Written Response</u>**

Where the court finds that the petition for review has the merit, court shall give to the agency against whom a petition of review had been filed an opportunity to submit a written response with 15 days.

**55. <u>Submission of Records,</u>**

The court may order the agency against whom a review petition is being considered to submit records relating to the directive or administrative decision under consideration.

## ንዑስ ክፍል አራት

## የክለሳ ዉሳኔ አሰጣጥ እና አፈፃፀም

**፶፮. የክለሳ ዉሳኔ አሰጣጥ**

፩/ ፍርድ ቤቱ የክለሳ አቤቱታውን በተቻለ መጠን በአጭር ጊዜ ውስጥ መርምሮ ዉሳኔ መስጠት አለበት፡፡

፪/ ፍርድ ቤቱ የክለሳ አቤቱታ የቀረበበትን የአስተዳደር መመሪያ ወይም ዉሳኔ ሊያፀና ወይም በሙሉ ወይም በከፊል ሊሽር ይችላል፡፡

፫/ ፍርድ ቤቱ የክለሳ አቤቱታ የቀረበበትን የአስተዳደር መመሪያ ወይም ውሳኔ በሙሉ ወይም በከፊል ሲሽር የአስተዳደር ተቋሙ በፍርድ ቤቱ ውሳኔ የተጠቆሙ ግድፈቶችን አስተካክሎ መመሪያውን እንደገና እንዲያወጣ ወይም እንዲያሻሽል፣ ወይም ውሳኔ ሰጥቶበት የነበረውን ጉዳይ እንደገና መርምሮ እንዲወስን ሊያዘው ይችላል፡፡

**፶፯. የክለሳ ዉሳኔ አፈፃፀም**

፩/ በፍርድ ቤት የተሰጠ የአስተዳደር መመሪያን ወይም ዉሳኔን የማፅናት ወይም የመሻር ውሳኔ ወዲያዉኑ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

፪/ ፍርድ ቤቱ የአስተዳደር መመሪያው ወይም ውሳኔው እንዲሻሻል ካዘዘ የአስተዳደር ተቋሙ በዚህ አዋጅ ክፍል ሁለት እና ሦስት የተመለከቱትን የሥነ-ሥርዓት ድንጋጌዎች እና መርሆዎች አክብሮ መመሪያውን ወይም የአስተዳደር ውሳኔውን በተገቢዉ ጊዜ ማሻሻል አለበት፡፡

## SUB-SECTION FOUR

## DECISION OF JUDICIAL REVIEW AND EXECUTION

**56. Judgment of Judicial Review**

1/ The Court shall investigate the petition of review and render its decision within the shortest possible period of time.

2/ The Court may confirm; or partially or fully reverse the administrative decision or directive submitted for review .

3/ Where the court renders a decision which partially or fully invalidate the administrative decision or directive, it may also order the administrative agency to revise or reenact the directive or reconsider its administrative decision by rectifying the shortcomings identified through the court's decision.

**57. Execution of the Decision**

1/ The decision of the Court to uphold or invalidate a directive or and administrative decision shall be executed immediately.

2/ Where the Court renders a decision for the revision of an administrative decision or directive, the administrative institution shall do the same in an appropriate time, by giving due consideration to the Provisions provided under Chapters Two and Three of this Proclamation.

፫/ በፍርድ ቤቱ የተሰጠ የአስተዳደር መመሪያን ወይም ዉሳኔን በሙሉ ወይም በከፊል የመሻር ዉሳኔ ወይም የማሻሻል ትዕዛዝ የክለሳ አቤቱታ የቀረበበትን መመሪያ ወይም ውሳኔ ሕጋዊ ኃይል በሙሉ ወይም በከፊል ያስቀራል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተገለጸው ቢኖርም፣ ፍርድ ቤቱ አንድን የአስተዳደር መመሪያ በከፊልም ሆነ በሙሉ የሚሽር ወሳኔ ሲሰጥ፣ የአስተዳደር ተቋሙ መመሪያው ከመሻሩ በፊት በተሻረው መመሪያ መሰረት የሰጣቸው አስተዳደራዊ ውሳኔዎቸ እንደጸኑ ይቆያሉ።

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፶፰. የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ተፈፃሚ ስለመሆኑ**

በዚህ አዋጅ ክፍል አራት ባልተመለከቱ የክለሳ ሥነ-ሥርዓት ጉዳዮች ላይ አግባብነት ያላቸዉ የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

**፶፱. የጉዳት ካሣ ስለመጠየቅ**

ከአስተዳደር መመሪያ ወይም ውሳኔ ጋር በተያያዘ ጥፋት ምክንያት ጉዳት የደረሰበት ማንኛውም ሰው መመሪያውን ያወጣው ወይም ውሳኔውን የሰጠው የአስተዳደር ተቋም አግባብ ባለዉ ሕግ መሠረት ካሳ እንዲከፍለው የመጠየቅ መብት አለው፡፡

**፷. መረጃ የመስጠት ግዴታ**

ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም ከመመሪያ ማውጣት ወይም ከአስተዳደር ውሳኔ መስጠት እና እነዚህን ከመፈጸም ጋር በተያያዘ በሌላ ህጋዊ አካል ሲጠየቅ መረጃ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

3/ The judgment of the Court fully or partially invalidating a directive or administrative decision, or an order of amendment shall, either fully or partially, revoke the legality of such directive or decision.

4/ Notwithstanding the rule under Sub Article (3) of this Article, decisions of an administrative agency made on the basis of a revoked directive prior to the ruling of the court shall stay valid.

## SECTION FIVE

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

**58. Applicability of the Civil Procedure Code**

On procedural matters not covered by Chapter Four of this Proclamation, the relevant Provisions of the Civil procedure Code shall apply.

**59. Compensation**

A person who has incurred damage as a result of a fault committed through issuance of directives or an administrative decision is entitled to seek compensation from the administrative authority that is responsible, in accordance with the relevant laws.

**60. Duty to Provide Information**

Where any administrative agency is requested to provide information relevant in the issuance of directives or rendering of administrative decisions by legal organ, such agency shall provide the information.

**፷፩. <u>ደንብ የማውጣት ሥልጣን</u>**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልግ ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፷፪. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መጋቢት ፳፱ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም**

**ሣህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ**

**ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**61. <u>Power to Issue Regulation</u>**

The Council of Ministers may issue Regulations that might be necessary for the proper implementation of this Proclamation.

**62. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazettee.

**Done at Addis Ababa, On the 7th Day of April 2020.**

**SHALEWORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC**

**REPUBLIC OF ETHIOPIA**